# ፍትህና ዓምደኞቹን በጨረፍታ (ሶስት)

**ዮናስ** 4/5/12

የተመስገን ደሣለኝን ርዕስ ዛሬም ተጠቅሜ የፍትህና አምደኞቹን ጨረፍታዬን ቀጥያለሁ፡፡ ርዕሱን ለመኮረጅ የተገደድኩት ደግሞ በ”ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ” አንድ ላይ እንደጠቆምኩት ከአሪፍ ቢኮረጅ አይከፋም የሚለውን የክቡር አቶ ግርማ ሰይፉ ብሂል በመውሰድ ነው፡፡ ተመሥገንም “የጠቅላይ ሚንስትሩን አማካሪዎች በጨረፍታ” ሲል ያስነበበን ተከታታይ ጽሁፍ ምንም እንኳ ውስጡ በአሉባልታ የታጨቀ በመሆኑ ይዘቱን ባልኮርጅም ርዕሡ አሪፍ ሆኖ ስላገኘሁት ከ"አሪፉ አዘጋጅ" ርዕሡንና ተከታታይነቱን ኮርጃለሁ፡፡ ቅንፎችን ደግሞ ከአቤ ቶክቻው መዋሴንም እትርሱብኝና ወደ ዛሬው ሃሳቤ ልረማመድ፤አብረን እንዝለቅ፡፡

በክፍል አንድ ጨረፍታዬ ፍትህን እንደጋዜጣ አዘጋጆቹን ደግሞ እንደባለሙያ (ጋዜጠኛ) አምደኞቹን ደግሞ እንደ… ከመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ከወጣው አዋጅና ከፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ አንፃር ጨረፍታ ነውና ቃኝቼአቸዋለሁ፡፡ ባጠቃላይ በነፍትህና አምደኞቹ በመንግስት የሚወጡ ህጎችና ደንቦች ሁሉ ፀረ ህዝብና ፀረ ህገመንግስት ስለመሆናቸው ነበረ ጨረፍታዬ፡፡ ለነዚህ ግለሠቦች ህገመንግስቱ ትርጉም የሚኖረው አዋጅ በወጣ ጊዜ እንጂ "ህገመንግስቱ ከተፃፈበት ወረቀትና እስኪሪፕቶ በላይ ዋጋ የሌለው" እንደሆነ፣ አንዳንዴም "ህገ አራዊት" ስለመሆኑና፤ ጋዜጣውና አምደኞቹ ህግንና ህገመንግስቱን በማጣቀስ ማወናበድ ዋነኛ ባህሪያቸው እንደሆነም፣ ይህ ደግሞ የሁሉን ታገኛለህ ወይ ሁሉን ታጣለህ ዘማሪያን ተፈጥሮ መሆኑን ለማውሳት ሞክሬያለሁ፡፡

ተመሥገን ጨረፍታውን አንድ ብሎ ጀምሮ እስከ አራት እንደሄደው ሁሉ፤ የፍትህ ቋሚ አምደኛ የሆኑት ፕሮፈሰር መስፍን ወልደማርያም መሬት አንድ ብለው በጋምቤላ መሬትና ኢንቨስትመንት አቆራርጠው መሬት ሁለት ወደሚለው የሊዝ አዋጅ እንዳቀኑት ሁሉ እኔም ዛሬ ፍትህና አምደኞቹን በጨረፍታ  ሶስት በሚል ወጌን እቀጥላለሁ፡፡

የዛሬው የፍትህና ዓምደኞቹ ጨረፍታዬ የአረቡ አለም አብዮትንና የኑሮ ውድነትን በመንተራስ ፍትህና አምደኞቹ ስለሽብር የነበራቸውን ጉጉት ከሽብርተኝነትና ከሚዲያ ግንኙነት አንፃር የሚፈተሽ ነው፡፡ ፍትህና አምደኞቹን ከላይ ከጠቀስኩት ርዕሰ ጉዳይ አንፃር ከመጨራረፌ በፊት ጨረፍታዬን ተጨባጭ ለማድረግ ይረዳኝ ዘንድ ጋዜጣዋና አምደኞቹ አስፈላጊ ሆነው ሲያገኙት ብቻ የሚጠቅሱትን፤ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ደግሞ የህጎች ሁሉ የበላይ መሆኑንና የሉዓላዊነታችን መገለጫ መሆኑን የሚቀበሉት ህገ መንግስት መረጃ ከማግኘት፣ ከመፃፍና ከመናገር ነፃነት አንፃር

ምን ይላል? ስል እጠይቅና በተከታይነት የሽብርተኝነትንና የሚዲያን ግንኙነት በተመለከተ የቀረበን አንድ ዓለም አቀፍ ጥናት በዋቢነት አቀርባለሁ፡፡

የህገ መንግስታችን ክፍል ሁለት ስለዴሞክራሲያዊ መብቶች ህገመንግስታዊ ዋስትና ያትታል፡፡ አንቀጽ 29 "የአመለካከት እና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት" በሚል ርዕስ ሰባት አንቀፆችን ይዟል፡፡

ፍትህና አምደኞቹ በዚህ ርዕስ ስር ከተጠቀሱት ሰባት አንቀጾች ውስጥ ስድስተኛውን እና ሰባተኛውን አንቀጽ ከቶውንም ቢሆን እንስተው አያውቁም ማንሳትም አይፈልጉም፡፡ ከአንቀጽ አንድ እስከ አንቀጽ አምስት ድረስ የተዘረዘሩት መብቶች ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ፣ ለመጻፍ፣ ለመናገርና የመሳሰሉትን ለማድረግ እንደሚችል እንዲሁም የፕሬስ ነፃነትና መረጃ የማግኘት መብት የተረጋገጡባቸው አንቀጾች ናቸው፡፡

"እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል፡፡ የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናሉ" ይላል፡፡ አንቀጽ ስድስት። አንቀጽ ሰባት ደግሞ "ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ ህጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል" ይለናል፡፡

የአረቡን አለም አብዮትና የኑሮ ውድነት በተመለከተ ፍትህና አምደኞቹን ከዚህ ድንጋጌ አንፃር ለጨረፍታ ወደኋላ እቃኛለሁ፡፡ አሁን ደግሞ ነገሬን ተጫባጭ ለማድረግ ይጠቅመኛል ወዳልኩት ሚዲያንና ሽብርተኝነትን ወደተመለከተው አለም አቀፍ ጥናት ልውሰዳችሁ፡፡

የጥናቱ ባለቤት በአሜሪካ አለም አቀፋዊ ጉዳዮች፣ የውጭ ጉዳዮች እና ብሄራዊ መከላከያ ክፍል የምክር ቤቱ ምርጫ ምርምር አገልግሎት ስፔሻሊስት የሆኑት ራፋኤል ኤፍ ፒል ናቸው፡፡ "ሽብርተኝነት ሚዲያና መንግስት፦ አተያዮች የተለመዱ አካሄዶችና ለፖሊሲ አውጪዎች የቀረቡ አማራጮች" Terrorism the media and the government perspectives, Trends and option for policy makers" P Raphael የጥናት ወረቀቱ ርዕስ ወይም ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡

ራፋኤል በዚህ ጥናታቸው ያረጋገጡት መሰረታዊ ነገር ሽብርተኞች ድርጊታቸው በሙሉ እንዲዘገብላቸው መፈለጋቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም የትኛውም ሽብርተኝነትን አስመልክቶ የሚሰጥ የሚዲያ ሽፋን ለአለም መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ በሽብርተኝነት አስተሳሰብ እርማት ያልተደረገበትን (Non- editing) የመሪዎቻቸውን መልዕክት በሚዲያ ማስተላለፍ እንደሽልማት

ይቆጠራል፡፡ ለምሳሌ በግንቦት 1997 CNN ከሳውዲ አረቢያው የፖለቲካ ተቃዋሚ፣ ሽብርተኞች መልማይና የገንዘብ ድጋፍ ሰጪው ከነበረው ኦሳማ ቢንላደን ጋር ያደረገው ቃለ ምልልስ ለዚህ ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሽብርተኞቹ ስኬት ነው፡፡

ሽብርተኞች ከድርጊታቸው ይልቅ ምክንያታቸው እንዲወራላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ማንም ሰው ድርጊታቸውን እንደሚቃወመው ስለሚያውቁ የፈጸሙበትን ምክንያት በመግለጽ የህዝቡን ድጋፍ ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ ህዝቡ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው በመጥፎና በጉልበተኞች እጅ እንደወደቀ፣ ብቸኛው አማራጭም ሽብር እንደሆነ ማስረዳት ስለሚፈልጉ ሚዲያዎችን ለይተው ቅንፍ የኔ (እንደፍትህ አይነቶቹን እና አምደኞቻቸውን) ጥሩ ግንኙነት ይመሰርታሉ ይላል የራፋኤል ጥናት፣ ጥሩ ግንኙነት መመስረት ብቻ አይደለም ሲሉ ራፋኤል ሽብርተኝነትን በተመለከተ በሶስተኛ ደረጃ ያስቀመጡት ደግሞ በገንዘብ አቅማቸው የተዳከሙ፣ በፖለቲካ ሥርዓቱ የተበሳጩ ጋዜጠኞችን (Sympathetic personal) ፈልገው በማግባባት ይደልሏቸዋል፣ይደጉሟቸዋል፣ብሎም ትንንሽ የዜና ተቋማትን ይመሰርታሉ፡፡

ሌላውና አራተኛው የሽብርተኞች ፍላጎት ዕውቅናን መፈለግ ነው የሚለን የራፋኤል ጥናት፡፡ በተለይም በሚቃወሟቸው ዘንድ የሚፈጠረውን ልዩነትና መከፋፈል በሚዲያ በማስነገር የነሱን ህጋዊነትና አስፈላጊነት ማጉላት ይፈልጋሉ፡፡ ሽብርተኝነታቸው በርዕዮተ ዓለማቸው እንዲዋጥ በማድረግ ህዝቡን ማስከተል ይፈልጋሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ማሳያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፍትህንና ዓምደኞቻቸውን የሚገልጻቸውና ለጨረፍታዬ እንደ ጥሩ ማሳያ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው የራፋኤል ጥናታዊ ግኝት ደግሞ ተከታዩ ነው፡፡

ሽብርተኞች መንግስት ላይ ክስረት ለማምጣትና መንግስትን የሚያዳክም መረጃ ለማቀበል ሚዲያውን (እንደፍትህ ዓይነቶቹን) ቅንፍ የራሴ ይጠቀሙበታል፡፡ በተለይ ይህ ነገር የሚዘወተረው ወንጀሉን የሚፈጽሙበት በቂ ምክንያት ሲያጡ ነው ይላል ጥናቱ፡፡ ያኔ ሚዲያው (እንደፍትህ አይነቱና ዓምደኞቹ) ፍርሃት በማስተጋባት ስጋት በማሰራጨት፣ የኢኮኖሚ ድቀት እንዲፋጠን ለምሳሌ የኢንቨስትመንት እና የቱሪዝም መስኩን ለመጉዳት ህዝብ መንግስት ላይ አመኔታ እንዲያጣ ለማድረግ ተግተው ይንቀሳቀሳሉ፣ እያለ ይቀጥላል ጥናታዊ ጽሁፉ፡፡

ከህገመንግስታችን አንቀጽ 29 የወስድናቸውን አስረጅዎችና ከራፋኤል ጥናት ያየናቸውን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ፍትህና አምደኞቹን ስንጨራርፋቸው እውነታው የቱጋ እንደሆነ የሚገለጽ ይመስኛል፡፡

ፍትህ ዛሬ ገበያ ውስጥ ሞልታለች፡፡ በኮፒ ብዛትም ገበያውን እየመራች ስለመሆኗ በራሷ ጋዜጠኞችና ዓምደኞች ተነግሮናል፡፡ አዟሪዎችና አከፋፋዮችም ከፊት አስቀድመው ይይዟታል፡፡ የአዟሪዎች ከፊት አስቀድሞ መያዝ የገበያ ጉዳይ ነው፡፡ ዳሩ ግን እነሱ ይህን የሚያደርጉት ከላይ

በራፋኤል ጥናት እንደተገለፀው ጽሁፋቸው ሁሉ ህዝብ በእጅጉ የተጎዳና የተበደለ በማስመሰል መንግስትን ለማዳከም የሚወጣውን ጽሁፍ እውነት መስሎት እንዲቀበል ለማድረግና በዚህም በቀላል የመደመር--መቀነስ የሂሳብ ስሌት ስውር አላማቸውን ለማራመድ አጋጣሚውን ለመጠቀም በማሰብ ነው፡፡ ዕለተ አርብ ለንባብ የምትበቃው ፍትህ "በፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳይ ላይ የምታተኩር" የሚል የህግ ተቀጽላ ይዛ ነው፡፡ በረጃጅምና በወፋፍራም ፊደላት ከታጀቡት_የፊት ገጽ ርዕሷ ስር የመንግስት ባለስልጣናት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት አልያም አንገብጋቢ የፖለቲካ አጀንዳን የሚያሳይ ካርቱን ወይም ቅንብር ፎቶ በጉልህ ያኖራሉ፡፡

ለማሳያ ያህልም ("ልማታዊ ሎሌዎች"፣ "መጅሊሱና ሲኖዶሱ"፤ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አጥማቂዎች"፣ "ሰላማዊ ትግል አበቃለት"..... በሚል ርዕስ ስር የወጡትን ምስሎች እዚህ ጋ ልብ ይሏል) ሌላም ማንሳት ይቻላል፡፡ "ሽብርተኛው ኢህአዴግ"፣ "የህዳሴው ግድብ ቀጣዩ ፈተናዎች"፣ "ከ6 ሚሊዮን በላይ ዜጎች በረሃብ ጥላ ስር"፣ "ፓርላማው ሞተ"፣ "ፋይዳ ቢሱ የታክሲ ዞን ስምሪት"፣ "አሸማቃቂው የሽብርተኝነት አዋጅ"፣ ቱንዚያ፣ ግብጽ ሊቢያ ቀጥሎስ?" የሰሞኑ ደግሞ "የተከበሩ ጨኸቶች-- ቡአዚዝ፤ መጅሊስና መምህራን ---" የሚሉት ርዕሶችና ጽሁፎች "ላም ባልዋለበት....." እንዲሉ የፍትህና የአምደኞቹ የሽብር ጥሪና መርዶ ነጋሪ አዋጆች ናቸው፡፡

እነዚህን ርዕሶችና ይዘታቸውን ተመልክተን ከህገመንግስታችን አንቀጽ 29 አንፃር ካየናቸው በአንቀጽ ስድስትና ሰባት የሰፈሩት ድንጋጌዎች "ኧረ የህግ ያለህ!!" በሚያስብል ደረጃ በፍትህና አምደኞቹ በግልጽ መጣሱን መረዳት እንችላለን፡፡

ሌላው የነዚህ አምደኞችና ጋዜጣዋ ጉድ ለጥቅም የተገዙ መሆናቸው ነው፡፡ መንግስት ላይ ክስረት ያመጣልናል፤መንግስትን ለማዳከም ይረዳናል በሚል የማደናቆሪያ ስሌት ራሱን ከህግ በላይ የተቀመጠ አስመስሎ የተኮፈሰው ፍትህ ጋዜጣና አምደኞቹ የራፋኤል ጥናት እንዳረጋገጠው  ሃሰተኛ ውንጀላና ክስ ማሰማት፤ጥላቻ መዝራት፤ፍርሃትና ሽብር ማስተጋባትና የግጭት መንስኤ ሊሆን የሚችል ስጋትና ጥርጣሬ ማሰራጨት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫቸው ነው፡፡

ሞራላዊ ባልሆነ መንገድ ኢጃብ ጠምጥሞ  ከስር መስቀል የያዘ የፎቶ ቅንብር፤  አጥንቱ ያገጠጠ ህፃን፣ ተቀጣጣይ ነገር በእጁ የያዘ የአረብ ወጣት...... የተመስገንና ዓምደኞቹ የርዕሥ ማጀቢያና የጋዜጣ ማሻሻጫ ተደርገው ከተወሰዱ የምስል ቅንብር ምርጫዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ጥቂት አጫፋሪዎቻቸው በባዶ እርካታ፤የሚነቅፏቸው ደግሞ "ዛሬ ደግሞ ምን ብለው ይሆን?" በሚል ስሜት ውስጥ ሆነው  በዚህም ሆነ በዚያ ጋዜጣው የገኘውን ቀልብ ስቦ እስከተሸጠ ድረስ ትርጉሙና አፍራሽ መልዕክቱ የፈለገውን ቢሆን እነሱ ምን ገዷቸው ይጨነቃሉ፡፡

ከምርጫ 2002 በኋላ በተመለከትኳቸው የፍትህ ጋዜጦች ገንቢ ሃሳብ፣ ቅን ሂስ፣ አሻሻይ ጥቆማ፣ የተለየ አተያይ ማግኘት ተስኖኛል፡፡ዋና አዘጋጁ-ን ጨምሮ ዜና ዘጋቢዎቹና  ዓምደኞቹ ሁሉ

መሽቶ በነጋና ዓርብ በመጣ ቁጥር የሚያዜሙት ስለ አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡  የተሰራውን ጥሩ ነገር እውቅና በመስጠትና በማድነቅ፣ እንዲሁም በዋናነት እውነታንና ተጨባጭ ሁኔታዎችን ተመርኩዞም ግድፈቶችንና፣ ስህተቶችን... ነቅሶ በመለዬት በሰለጠነና ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ገዥውን ፓርቲ በመንቀፍ በእርግጥም መሻሻልና መስተካከል ያለባቸውን  ጉዳዮች በገንቢ አስተያዬት ያነሳሉ ብዬ እንዳልናገርም ሁሉም ፀሃፊዎች አንድ አይነት ነገር ነው ይዘው የሚወጡት አመጽና የአመጽ ጥሪ ብቻ፡፡ ከላይ የጠቃቀስኳቸውን በማድረግ ለህዝቡና ለሃገሪቱ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ካልቻሉና ካልፈቀዱ ደግሞ ሌላው ስራውንና ተግባሩን እንዲወጣ ቢያንስ ቢያንስ ዝም ማለት ቢችሉ አንድ ነገር ነበር፡፡ ነገረ ስራቸው ሁሉ አንድ ቅብጥብጥ ህጻን ብላ ሲሉት እምቢ፣ተወው እሺ ሲሉትም እምቢ እንደሚለው አይነት ከሆነ እኮ ሰነበተ፡፡

የኑሮ ውድነት በተለያየ ምክንያት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ዋናው ነገር ይህን ችግር ለመፍታት የመንግስት ጥረት ምን ያህል ነበር? ብሎ ማየትና የችግሩም የመፍትሄውም አካል ሆኖ መገኘት እውቀት ነው፡፡ ግን ዓላማቸውና መነሻቸው የዜሮ ድምር ፖለቲካ በመሆኑ የመንግስትን ጥረት ማጣጣልና ማጠልሸት ዋነኛ ስራቸው ነው፡፡ ቀደም ብለው ኑሮ ተወደደ ህዝብ ተቸገረ ብለው ያወሩና ችግሩን የተመለከተው መንግስት ሊፈታ ሲንቀሳቀስ ደግሞ ጣልቃ ገባ ሲሉ ክሳቸውን በየዓምዶቻቸው  በአምደኞቻቸው ያስተጋባሉ፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን የአዲስ አባባውን ሲናገሩ፣ ሃይለመስቀል የጋምቤላውን ፣ተመስገን ደግሞ ሌላውን አቶ አሰገደ ሲቀጥሉ የትግራይ ህዝብ በረሃብ መቆላቱን በመፃፍ የዱላ ቅብብሎሽ ሽብራቸውን ይነዛሉ፡፡

አንዳንዴ ደግሞ ሙያዊ ክፍተታቸውን የእውቀትና የጥበብ ጉድለታቸውን መንግስት አላሰራ አለን፣ ህገ መንግስቱ የሰጠንን መብት ነፈገን፣ ጋዜጠኞቻችን ታሰሩብን በሚሉ ክሶች ሊያድበሰብሱ ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ዳሩ ግን የፍትህና አምደኞቹን ጀርባ ለማየት ባደረኩት ጥረት የደረስኩበት ነጥብ የባዕድ እጅ ደግፏቸው የጠላት ገንዘብ ኪሳቸውን መሙላቱን ነው፡፡ ኧረ እንዳውም ስማቸውንና ፎቶ ግራፋቸውን በማከራዬት "ምርጥ" የተባሉ ጽሁፎችን በአንዳንድ "ምርጥ" ቅጥረኞች ወይም ስፖንሰሮች ጭምር እንደሚያጽፉ ሁሉ ይታወቃል፡፡ ይህን ደግሞ ተመስገንና አምደኞቹ ቢያንሰ ህሊናቸውን ሊዋሹ ስለማይችሉ በትክክል ያውቁታል፡፡ ስለሆነም ፍትህና ዓምደኞቹ አላዋቂነትንና ሕገወጥነትን ከግልብነት ጋር አዋህደው በመጓዝ ላይ ናቸው፡፡ ከምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ለተቀመጠችው ሀገራችን አልሸባብን ጨምሮ ሌሎችን ከውስጥም ከውጭም  የጸረ-ሰላም ኃይሎችን ያሰባሰበው የኢሣያስ አፈወርቂ መንግሥት ናቅፋ እስከፍትህ ቢሮና ዓምደኞቹ ኪስ አይደርስም ማለት አይቻልም፣ይህ ባይሆን እመኛለሁ፣እኔ ግን በበኩሌ ጠረጠርኩ፣በርካታ ማሳያዎች አሉኝ፡፡

የፍትህና ዓምደኞቹ ሽፋናቸው "ሚዛናዊ ዘገባ" የሚል ነው፡፡ ነገር ግን ከየድረ ገጹ የሚቀበሏቸውን ከአመጽና ሽብር ጋር የተያያዙና ሽብርን የሚያበረታቱ “ጥናታዊ” እና ”የምርምር” ጽሁፎች ገልብጠው ሲያትሙ የህገመንግስቱን አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 ድንጋጌዎች ማስታወስ አይፈልጉም፡፡ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የሃገሪቱ ሕጎች ሁሉ አሳሪና የማያሰሩ ናቸው በማለት ባዶ

ጩኸታቸውን ማስተጋባት የሚጀምሩት፡፡ አንዳንድ የእርዳታ ድርጅቶች ይፋ የሚያደርጓቸውን የ"ጥናት" ውጤቶች ተርጉማችሁ ጋዜጣችሁ ላይ ስታወጡ ምን እያሰባችሁ እንደሆነ ይገባናል፡፡ የተከፈላችሁን ውለታ፤የበላችሁትን ቀብድ፤ አለያም ቃል የተገባላችሁን ጥቅም ወይም ሌላ.....በማሰብ ሂሳባችሁን ለማወራረድ? ቀሪውን ምላሽ ለናንተው እተዋለሁ፡፡

ትግሉ ከቃላት ወደ ተግባር መሸጋገር እንዳለበት መሽቶ በነጋ ቁጥር የሚያሳስቡት ፍትህና የፍትህ አምደኞች ምርጫ 97 ላይም የአመጽና የሁከት ምድጃውን ቆስቁሰው ወጣቱን ውኻንብር ውስጥ ከተው በጋለው ምጣድ ላይ ከጣዱት በኋላ እንደ ጲላጦስ "እኔ የለሁበትም፤አልሰማሁም፤አላዬሁም፤በስፍራው አልነበርኩም...." ብለው ያፈገፈጉ ኃይሎች ናቸው፡፡ በጸረ ሕዝብ ድርጊታቸው ጃስ ሲሏቸው ቀኝ ኋላ ዙረው የሚሮጡ ሃይሎች በየትኛው ሞራላቸው እንደሆነ ለኔ ባይገባኝም ሁሌም ለወጣቱ የአገር አፍርስ ጥሪ "ጀግንነትን" እየሰበኩ ነው፡፡

በጣም ከሚገርመኝ የፍትህ አምደኞች ተፈጥሮ መሀከል ትናንት ስለተናገሩት ማስታወስ አለመሻታቸው ነው፡፡ ምሣሌ ማቅረብ እችላለሁ፡፡ እስክንድር ነጋ በህይወት ታሪኩ ኢትዮጵያ የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀገር መሆኗን ሲናገር አላደመጥኩም፣ፅፎም አላነበብኩም፡፡ ነገር ግን የአረቡን አለም አብዮት እንደጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም አመፅ ለመቀስቀስ ሲፈልግ የግድ የኢትዮጵያን ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልብ ማግኘት የግድ ይለው ነበርና ጳጉሜ 4/2003 በወጣችው ፍትህ ጋዜጣ ላይ የኢትዮጵያ ስልጣኔ የብሄር ብሄረሰቦቿ የጋራ ውጤት መሆኗን አስነበበን፡፡ በዚህ ቢያበቃ ጥሩ፤ አንዲት ሀገር አንድ ባንዲራ እና አንድ ቋንቋ ሲለን እንዳልነበር የኢትዮጵያ ሥልጣኔ የብሄር ብሄረሰቦቿ የጋራ ውጤት መሆኑን ከነገረን በኋላ ኢትዮጵያ በታሪኳ አንድ ቋንቋ የሚነገርባት አንድ ሃይማኖት የሚመለክባት ሀገር ሆና አታውቅም ብሎን ልባችንን ሊገዛ ሞከረ፡፡ እኛ ግን ይሂ ሽርደዳ ነው፤ ሌላ ብላ ብለን መለስንለት፡፡

የፍትህ ጋዜጣ አምደኞች በብዙ ባህሪያቸው በህገ ልቦናም ጭምር አንድ ናቸው፡፡ ሽብርተኝነትና ዓመጽ አንድ ያደረጋቸው ናቸው ያልኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ እስክንድር በኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና ቋንቋ ላይ እንዳላገጠ ሁሉ አቤ ቶክቻውም ለህዳሜው ግድብ የተለያየ ስም ሲሰጥና በተጨባጭ የማይታይ ማስቀየሻ አድርጎ ሲስለው እንደከረመ የምናስታውሰው ነው፡፡ ዛሬ ግን የህዳሰው ግድብ እውን ሲሆንበት መፀነሱን ያልተቀበለው አቤ ቶክቻው በመጋቢት 21/2004 ወጉ የህዳሴው ግድብ እንደተወለደ አበሠረን፡፡

ብሥራትን ግን አቤ ፈልጎ አይደለም ያበሰረን። የህዳሴው ግድብ ኪሳችንን እያራቆተ መኖርን እንድንጠላ ሊያደርገን ነው በሚል ህዝብን ለመቀስቀስ መጀመሪያ ግድቡ በተጨባጭ መኖሩን ከመቀበል መጀመር አለበትና መወለዱን አመነልን። የማንዘር ጎመን ዘር እንዲሉ እስክንድርም አመፅ ለመቀስቀስ ቢጠቅመኝ ብሎ በማሰብ መጀመሪያ ከአንድ ብሄር አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት መውጣት ስለነበረበት ነው ቀደም ብዬ የጠቀስኩትን የፃፈልን።

የአቤ ቶክቻው አስቂኙ ዜማ ደግሞ 80 ቢሊዮን ብርን ለ7 ቢሊዮን (የዚህ አመት ገቢ) አካፍሎ ግድቡን ለመጨረስ 11 አመት ይፈጃል ማለቱ ነው። የፕሮጀክቱን ጥንስስ ብስራት በመስማቱ ብቻና በቀጣይም ይህንንም ተከትሎ ባየው የተግባር እንቅስቃሴ ከ7 ቢሊዮን ብር በላይ በራሱ ፈቃደኝነትና ተነሳሽነት ያዋጣ ህዝብ ከዚህም በላይ ሊያደርግ ወይም ተአምር ሊፈጥር እንደሚችልስ መገመት ለምን ከበደህ? ሳታውቀው ቀርተህ ነው ብዬ አልልም፡፡ ስጋት ዘርተህ  ውድቀት ለማጨድ ካለህ ጨለምተኛ አመለካከትና ክፉ ምኞት የመነጨ ሆኖብህ እንጂ።

ሁሉም እንደዚሁ ናቸው፡፡ መጋቢት 21/2004 ለነፍትህና ዓምደኞቹ የተመቸ ሰሞን ሆኗል፡፡ ለምን ቢባል የመምህራን የደሞዝ ጥያቄ አለላቸው፡፡ ማራገብ ልማዳቸው ስለሆነ የዙቋላን ገዳም የእሳት ቃጠሎ ትንፋሽ በማዋጣት ጭምር እንዳይጠፋ እፍ ሲሉት ከረሙና የመምህራኑን ሰላማዊ የመብት ጥያቄ ከቡአዚዝና ከአረቡ አለም ጋር አገናኝተው በግድ ለጠፉት። የውኸርንብር አጀንዳቸውንም እንደ ኳስ በመቀባበል ፕሮፌሰሩ ከሦሪያው ዓመጽ ጋር አያያዙት፤ ሃይለመስቀል በሸዋም የለህ ደግሞ "ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል" በሚል ጥሪውን አስተላለፈ፡፡

በጊዜ ለኩሉ አምዳቸው ደግሞ «እናንተ ኢትዮጵያውያን በሠይፌ ትገደላላችሁ» ሲሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስን አስነብቦን ለሰሞኑ አሳረገው፡፡ ዓለማየሁ ገላጋይም "የሁለት ሥልጡን ህዝቦች ወግ" ሲል ያስነበበን ለኔ ትርጉሙ አመጽ ነው፡፡ በዳንኤል ተፈራ የቀረበው "የትናንት ወጣት የዛሬ ወጣትና መጪው ጊዜ"ም ሌላው የትርምስ ጥሪ ደውል ነው፡፡ ምን ይኸ ብቻ "የተባበሩት ጩኸቶች" ደግሞ ትክክለኛው የፍትህና የዓምደኞቹ የሽብርተኝነት መገለጫ ጽሁፍ ነው፡፡

የፀረ ሽብርተኝነቱ አዋጅ፤ “የሽብር ወንጀል እንዲፈጸም የሚደረግ ማበረታታት ቅስቀሣና ማወደስ፣ በንግግር በጽሁፍ፣ በምስል ይኸውም በጋዜጣ ሬዲዮ ቴሌቭዥን ድራማ መጽሃፍ በራሪ ወረቀትና ድረገጾችን መጠቀም በይዘቱ የሽብርተኝነትን አላማ ድርጊትን የሚያስተዋውቅና የሚያራምድ በመሆኑ ያስጠይቃል” ይሏችኋል፤፤ አዎ በእርግጥም ይህ የሕግ አንቀጽ እናንተ መሆንና እንዲሆንም በምትፈልጉት የአፍራሽነት አካሄድ አያሰራችሁም፤እንዲሆንም ሊፈቀድላችሁ አይገባም፡፡

እኔ ግን እላችኋለሁ ፍትህና ዓምደኞቹን፤ ጩኸታችሁ ሁሉ ከንቱ ጩኸት ነው፡፡ ቁመናችሁ ሁሉ ሰይጣናዊና አፍራሽ ነው፡፡ ሞራል የሌላችሁና የውጭ ቅጥረኞች መሆናችሁን ሁሉም ደርሶበታልና አትልፉ። ይኸው እናንተ ማላዘን ከጀመራችሁ ስንት ጊዜያችሁ ነው? በነዚህ ጊዜያት አገሪቷ የት እርቀት እንደደረሰች ማየት ከቻላችሁ ጩኸታችሁ ሁሉ የቁራ መሆኑን ትረዱታላችሁ፡፡

ሕዝቡ በተያያዘው የልማት ጎዳና ፍጥነቱን ጨምሮ ሲጓዝና እናንተ ደግሞ ወደኋላ ስትጎተቱ ባዶ ጩኸታችሁ ለሌሎች ይበልጥ እየራቀ ለራሳችሁ ብቻ የሚደመጥ ሆኖ በራሱ ስዓት መሰማት ሲያቆምና ሲከስም ታዩታላችሁ፡፡ ያኔ በሙታን መንደር የምናነበውን "ሩጫዬን ጨርሻለሁ…."

ብላችሁ ከነሕሊና ወቀሳችሁና የሕዝብ ትዝብት የምትናፍቁትን የዘላለማዊ ሃፍረት እረፍታችሁን ታገኛላችሁ፤ትውልዱም ታሪክ እየሰራ የማያቋርጥ ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ እኔም ጨረፍታዬን አራት በሚል እቀጥላለሁ፡፡